# በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች (FAQ): የሬኒየር ቢች ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ደህንነት

### 1. አዲሱ የሬኒየር ቢች ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ደህንነቱ የተጠበቀ ነውን?

አዎ።ትምህርት ቤቱ ደህንነቱ የተጠበቀ ነው። በቅርቡ በተደረገ ምርመራ **በህንፃው ውስጥ methane እንዳልተገኘ** አሳይቷል።**methane** ወደ ህንፃው እንዳይገባ የሚከላከሉ የደህንነት ስርዓቶች በህንጻው መሠረት ውስጥ ተገንብተዋል።

---

### 2. methane ምንድን ነው?

Methane በተፈጥሮ peat ባለው አፈር ውስጥ ሊፈጠር የሚችል ጋዝ ነው።

---

### 3. methane እንዴት አደጋ ሊያስከትል ይችላል?

Methane አደጋ ሊፈጥር የሚችለው በተገደበ ቦታ ውስጥ ሲከማች እና ከብልጭታ ወይም ከእሳት ጋር ሲገናኝ ብቻ ነው።methane በአግባቡ እንዲወጣ(vented) ከተደረገ የመቀጣጠል አደጋ አያስከትልም።

በቅርብ ጊዜ በተደረጉ ምርመራዎች በትምህርት ቤቱ ህንፃ ውስጥ methane አለመኖሩን አሳይተዋል።እንደ ቅድመ ጥንቃቄ፣ሲያትል የህዝብ ትምህርት ቤቶች የረጅም ጊዜ ደህንነትን ለማረጋገጥ ከህንጻው መሠረት በታች የመከላከያ እርምጃዎችን ገንብተዋል።በህንፃዎቹ ውስጥ ማንኛውንም methane ለመከታተል ምርመራው ይቀጥላል።

---

### 4. ሰዎች ስለ የትምህርት ቤት methane የሚያወሩት ለምንድን ነው?

ከትምህርት ቤቶች ህንጻ በታች ያሉ አንዳንድ አካባቢዎች peat ያለባቸው አፈር አላቸው፣እነሱም methane ሊፈጥሩ ይችላሉ።ይህ በአንዳንድ የሲያትል አካባቢዎች የተለመደ ነው።ስለዚህም ነው ሲያትል የህዝብ ትምህርት ቤቶች ከመጀመሪያ ጀምሮ የደህንነት መከላከያዎችን እና ምርመራዎችን የሚያቅደው።

---

### 5. ትምህርት ቤቱ ሲገነባ የተዘለሉ የደህንነት እርምጃዎች አሉ?

የሉም።**በግንባታ ወቅት የተለዩት ሁሉም የደህንነት እርምጃዎች ተካተዋል።**ይሁን እንጂ፣ትምህርት ቤቱ ከመከፈቱ በፊት የmethane ምርመራ መደረግ አለበት የሚለውን ምክረ ሃሳብ አልተደረገም።ያ ስህተት ነበር። ሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ምርመራውን ጀምረዋል፣እና በታህሳስ 2025 በተካሄደው ምርመራ በህንፃው ውስጥ ምንም methan እንደሌለ አረጋግጧል።

---

**6. በትምህርት ቤቱ ውስጥ የተገነቡ የደህንነት ስርዓቶች ምንድን ናቸው?**

ትምህርት ቤቱ የሚከተሉትን አለው:

- ከጣሪያው በላይ ጋዝን ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ የሚያስተላልፍ በህንፃው ስር የሚቴን የአየር ማናፈሻ ስርዓት(**methane venting system)**
- methane እና እርጥበትን የሚዘጋ ከህንጻው መሠረት በታች ወፍራም የውሃ መከላከያ(**thick waterproof barrier)**

እነዚህ የደህንነት እርምጃዎች methane ወደ ህንፃው ውስጥ እንዳይገባ ለመከላከል ይረዳሉ።

---

**7. ትምህርት ቤቱ የ methane ምርመራ ተደርጎለታል?**

አዎ።

- **በታህሳስ 9፣2025** የተደረገው ምርመራ በትምህርት ቤቱ ውስጥ ምንም አይነት **methane አለመኖሩን** አሳይቷል።
- የምርመራ መሳሪያዎቹ methan እና ሌሎች ተቀጣጣይ ጋዞችን ይፈትሻሉ።

---

**8. የmethane ምርመራውን ይቀጥላል?**

አዎ። ሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች የሚከተሉትን ያደርጋል፡

- የmethane ምርመራውን መቀጠል
- መደበኛ ምርመራ እንዲያደርግ የውጭ ባለሙያ መቅጠር
- የምርመራዉን ውጤቶች ለማህበረሰቡ ማጋራት

---

**9. የደህንነት ስራውን ማን ይፈትሿል?**

- **Maul Foster & Alongi (MFA)** የተባለ የአካባቢ ምህንድስና ድርጅት በታውን አጥንቶ የደህንነት ስርዓቶችን ይገመግማል
- **Building Envelope Technology Research (BET&R)** የተባለ የህንፃ ኤንቨሎፕ አማካሪ ድርጅት የውሃ መከላከያውን በትክክል መዘጋቱን ያረጋግል

---

**10. የአፈር አቀማመጥ(soil settling) ጉዳይስ?**

በግንባታው ወቅት፣ የሕንፃው ክብደት ሲጨመር አንዱን የአፈር ክፍል ከሚጠበቀው በላይ ወደ ታች( (settled)ተንቀሳቅሷል።

- ችግሩ ተፈትቷል
- ከተስተካከለ ወደ ታች የተንቀሳቀሰ (**settling**)ነገር የለም

---

**11. ሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች፣ትምህርት ቤቱ ደህንነቱ የተጠበቀ እንዲሆን አሁን ምን እያደረገ ነው?**

የሲያትል የህዝብ ትምህርት ቤት የሚከተሉትን እያደረገ ነው:

- የ methane ምርመራ መቀጠል
- ለተጨማሪ ግምገማ የውጭ ባለሙያዎችን መቅጠር
- መረጃ እና የምርመራ ውጤቶችን ለቤተሰቦች፣ለሠራተኞች እና ለማህበረሰቡ ማጋራት

---